መልእክት አሥራ-አንድ

## በእግዚአብሔር ልብ መሠረት የሆኑ እረኞች

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ ኤር. 2፡8፤ 3፡15፣ 10፡21፤ 23፡1-4፤ ኢሳ. 40፡11፤ ሕዝ. 34፡11-31፤ ዮሐ. 10፡11፤ ዕብ. 13፡20-21፤ 1 ጴጥ. 2፡25፤ 5፡2፣ 4፤ ራእ. 7፡16-17

**I. ያሕዌ እረኞችን፣ ገዢዎችን በተመለከተ በነቢዩ ኤርምያስ በኩል ተናገረ—ኤር. 2፡8፣ 10፡21፦**

ሀ. እረኞቹ፣ ገዢዎቹ፣ በያሕዌ ላይ አመጹ፤ ያሕዌን አልፈለጉም፣ መንጋቸውም ተበተነ—ኤር. 2፡8፤ 10፡21።

ለ. እረኞቹ የያሕዌን የማሰማርያ በጎች አጥፍተዋል፣ በትነዋልም—23፡1-2።

ሐ. ያሕዌ የመንጋውን ቅሬታ እንደሚሰበስብ እና ወደ መሰማርያቸው መልሶ እንደሚያመጣቸው እና በእረኝነት የሚንከባከቧቸው እረኞችን በላያቸው እንደሚያስነሣ፣ ፍሬያማም እንደሚሆኑና እንደሚበዙ ቃል ገባ—ቁ. 3-4።

መ. ያሕዌ በልቡ መሠረት የሆኑ እረኞችን ለእስራኤል ለመስጠት ቃል ገባ፤ እንዲህ ያሉት እረኞች ለእግዚአብሔር ሕዝብ የእግዚአብሔርን ተገቢ የሆነ እውቀትና መረዳት ይሰጣሉ—3፡15።

**II. ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን ሁለቱም በእግዚአብሔር ልብ መሠረት የሆነውን እረኛ ክርስቶስን ይገልጣሉ—ኢሳ. 40፡11፤ ሕዝ. 34፡11-31፤ ዮሐ. 10፡11፤ ዕብ. 13፡20-21፤ 1 ጴጥ. 2፡25፤ 5፡4፤ ራእ. 7፡16-17፦**

ሀ. ኃያሉ፣ ገዢውና ፈራጁ የሆነው ክርስቶስ እረኛ ለመሆን ይመጣል፤ ጠቦቶቹን በክንዱ በመሰብሰብ፣ በእቅፉ በመሸከም እና ግልገሎቹን የሚያጠቡትን በመምራት፣ በጎቹን በመግዛቱና በማስተካከሉ እና መንጋውን በመመገቡ ለመንጋው ይጠነቀቃል—ኢሳ. 40፡10-11፤ ማቴ. 2፡6፤ 9፡36።

ለ. ሕዝቅኤል 34፡11-31 እረኛ የሆነው ጌታ ራሱ በጎቹን ሊሻቸው እና ሊፈልጋቸው እንደሚመጣ ተንብዮአል፦

1. እንደ እረኛው፣ ጌታ ሕዝቡን፣ በጎቹን ከአሕዛብ መካከል አውጥቶ ይሰበስባቸዋል፣ ከሞት የተነሣውን እና የዐረገውን ክርስቶስ በሚያመለክቱት በረጅሞቹ ተራሮች ላይ ይኖሩ ዘንድ እንደ የእግዚአብሔር ሕዝብ እድልፈንታ ሁሉን-ያካተተውን ክርስቶስ በምሳሌ ወደሚያሳየው ወደ ከነዓንም ምድር መልሶ ያመጣቸዋል—ቁ. 11፣ 14።
2. ጌታ ኢየሱስ እንደ እረኛ ሊንከባከበን ሲመጣ፣ እንደ ንጉሥም ደግሞ ሊገዛን ይመጣል፤ እንደ እረኞችን ለእኛ ያለው የጌታ እንክብካቤ ውጤቱ እንደ ንጉሣችን እንድንታዘዘው እና በውስጣችን ወዳለው ንግሥናው እና ዙፋኑ ሥር እንድንመጣ ነው—ቁ. 23-24።

ሐ. ክርስቶስ መልካሙ እረኛ፣ ታላቁ እረኛ፣ የእረኞች አለቃ እና የነፍሳችን እረኛ ነው—ዮሐ. 10፡9-17፤ ዕብ. 13፡20-21፤ 1 ጴጥ. 5፡4፤ 2፡25፦

1. መልካሙ እረኛ የሆነው ጌታ ኢየሱስ ሕይወት እንዲሆንልን (እንዲኖረን) እና ሕይወት እንዲበዛልን (እንዲትረፈረፍልን) መጣ—ዮሐ. 10፡10-11፦
   ሀ. በጎቹ የእርሱን ዞዌ (Zoe) ሕይወት፣ መለኮታዊ ሕይወት ይካፈሉ ዘንድ ለበጎቹ ቤዛነትን ለመፈጸም፣ የነፍስ-ሕይወቱን፣ የሰብዕና ሕይወቱን አሳልፎ ሰጠ—ቁ. 11፣ 15፣ 17።
   ለ. በጎቹን ከበረት አውጥቶ ከእርሱ በነጻነት ወደሚበሉበት እና በእርሱ ተመግበው ወደሚጠግቡበት እንደ መሰማርያው፣ እንደ መመገብያው ሥፍራ ወደ ራሱ ውስጥ ይመራቸዋል—ቁ. 9።
   ሐ. ጌታ ከአይሁድና ከአሕዛብ የሆኑትን አማኞች በእረኝነቱ ሥር ወደ አንድ መንጋ (ወደ ቤተ ክርስቲያን፣ ወደ የክርስቶስ አካል) ውስጥ ሠርቷቸዋል—ቁ. 16።
2. "በዘላለም ኪዳን ደም ለበጎች ትልቅ እረኛ የሆነውን ጌታችንን ኢየሱስን" አምላክ ከሙታን አስነሣው—ዕብ. 13፡20፦
   ሀ. ዘላለማዊው ኪዳን አንድን መንጋ፣ የክርስቶስን አካል የምታመጣውን እና በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም የምትጠናቀቀውን ቤተ ክርስቲያንን ለማግኘት የሆነ የአዲሱ ኪዳን ቃል ኪዳን ነው።
   ለ. ታላቁ እረኛ የሆነው ጌታ የአዲሱን ኪዳን ይዘቶች እውን እያደረገልን ነው እንዲሁም በዕብራውያን መጽሐፍ ወደ ተገለጡት አዎንታዊ ነገሮች ልምምድ እና ድሰታ ውስጥ እየመራን ነው—8፡8-13፤ 1፡1-3፤ 2፡9-18፤ 5፡6-10፣ 14፤ 7፡16፣ 22፣ 24-26፤ 13፡1፣ 8፣ 12-15።
3. እረኞች አለቃ የሆነው ክርስቶስ በአብያተ ክርስቲያናት ሽማግሌዎች በኩል መንጋውን በእረኝነት ይንከባከባል—1 ጴጥ. 5፡4፦
   ሀ. ያለ ሽማግሌዎች እረኝነት ቤተ ክርስቲያን መገንባት አትችልም—ቁ. 2።

ለ. የሽማግሌዎች እረኝነት በእነርሱ በኩል የሆነ የክርስቶስ እረኝነት መሆን አለበት።

4. የነፍሳችን እረኛ የሆነው እስትንፋሳዊዉ ክርስቶስ ለውስጥ ማንነታችን ሁኔታ እየተጠነቀቀ በመንከባከብ የውስጥ ሁኔታችንን ለማወቅ ይቃኛል—2፡25፦
   ሀ. ለነፍሳችን ደህንነት ግድ በመሰኘት እና በውስጥ ማንነታችን ሁኔታ ላይ እይታውን በማንቀሳቀስ በእረኝነቱ ይንከባከበናል።
   ለ. ነፍሳችን በጣም የተወሳሰበች ስለሆነች፣ ነፍሳችንን በእረኝነቱ ለመንከባከብ፣ አእምሮአችንን፣ ስሜታችንን እና ፈቃዳችንን እንዲሁም ችግሮቻችንን፣ ፍላጎቶቻችንን እና ቁስሎቻችንን ለመንከባከብ በመንፈሳችን ውስጥ ያለው ሕይወትን-የሚሰጥ መንፈስ የሆነው ክርስቶስ ያስፈልገናል።
   ሐ. የነፍሳችን እረኛ የሆነው ጌታ ነፍሳችንን ይመልሳል ለነፍሳችንም እረፍት ይሰጣል—መዝ. 23፡3፤ ማቴ. 11፡28-30።

5. በወደፊት ዘላለም ክርስቶስ ወደ ሕይወት ውኃ ምንጮች የሚመራን የዘላለም እረኛችን ይሆናል—ራእ. 7፡16-17፦
   ሀ. የሦስታንዱን አምላክ ዘላለማዊ እደላ እንደሰት ዘንድ የዘላለም እረኛችን የሆነው ክርስቶስ እንደ የሕይወት ውኃ ምንጮች ወደ ራሱ ውስጥ ይመራናል—ቁ. 17።
   ለ. የሕይወት ውኃዎች አቅርቦት በዚያ ይሆናል፣ የእንባዎች ፈሳሽም ይታበሳል—ቁ. 17።
   ሐ. በዘላለም ውስጥ ባለው የክርስቶስ እረኝነት ሥር እንባዎች፣ ረሃብ፣ መጠማት አይኖሩም—ድሰታ ብቻ—ቁ. 16-17።

## III. ጌታ ኢየሱስ በምድር አገልግሎቱ የጀመረውን የእረኝነት እንክብካቤ በሰማያዊ አገልግሎቱ ቀጥሎታል—ዕብ. 13፡20-21፦

ሀ. በዮሐንስ 21፡15-17 (አ.መ.ት.) ጌታ ለጴጥሮስ እርሱ በሌለበት ጊዜ፣ በሰማያት እያለ፣ ጠቦቶቹን እንዲመግብ እና በጎቹን በእረኝነት እንዲንከባከብ (እንዲጠብቅ) ተልዕኮ ሰጠው፤ ይህም የእግዚአብሔርን መንጋ በእረኝነት ለመንከባከብ ሐዋርያዊውን አገልግሎት ከክርስቶስ ሰማያዊ አገልግሎት ጋር ለማካተት ነበር፦

1. ሰማያዊ አገልግሎቱን ለማከናወን እርሱ በሰማያት ሲያደርግ የነበረውን ሐዋርያት በምድር ላይ አደረጉት—ዕብ. 13፡20-21፤ ዮሐ. 21፡15፡17።
2. የእረኝነት እንክብካቤን በተመለከተ ሐዋርያዊው አገልግሎት ከክርስቶስ ሰማያዊ አገልግሎት ጋር ይተባበራል—ቁ. 15-17።

ለ. በሰማያዊዉ አገልግሎቱ ካለው ከክርስቶስ የእረኝነት እንክብካቤ ጋር በመተባበር ጳውሎስ ቅዱሳንን በእረኝነት የመንከባከብ ምሳሌ ነው—ዕብ. 13፡20-21፤ 7፡25-26፤ 1 ጢሞ. 1፡16፤ 2 ቆሮ.1፡3-4፤ ሐዋ. 20፡20፦

1. ጳውሎስ ልጆቿን እንደምትንከባከብ እናት እና ልጆቹን እንደሚመክር አባት ቅዱሳንን በእረኝነት ተንከባከባቸው—1 ተሰ. 2፡7-8፤ 11-12።
2. ጳውሎስ በኤፌሶን ያሉትን ቅዱሳን "በጉባኤም በቤታቸውም" በማስተማር (ሐዋ. 20፡20) እና ቅዱሳንን እያንዳንዳቸውን ለሦስት ዓመት በእንባ በመገሠጽ (ቁ. 31፣ 19) የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ በመንገር (ቁ. 27) በእረኝነት ተንከባከባቸው።
3. ለሚያገለግለው ሕይወት ጥብቅ ግድ መሰኘት ያለው ለመሆን ጳውሎስ በልቡ ሰፍቶ ነበር—2ቆሮ. 7፡2-3፤ 1ተሰ. 2፡8፤ ፊልጵ. 2፡19-20።
4. ጳውሎስ ደካሞችን ለመጥቀም (ለማግኘት) እንደ ደካሞች ሆነ—2 ቆሮ. 11፡28-29፤ 1 ቆሮ. 9፡22፤ ተዛ. ማቴ. 12፡20።
5. የቤተ ክርስቲያን አፍቃሪ የሆነው ጳውሎስ ከቤተ ክርስቲያን አፍቃሪው ክርስቶስ ጋር አንድ በመሆን የክርስቶስን አካል ለመገንባት ስለ ቅዱሳን ሲል ንብረቶቹን የሚያመለክተውን የነበረውን ለመክፈል፣ ማንነቱን የሚያመለክተውን እርሱ የሆነውን ለመክፈል ፈቃደኛ ነበር—ኤፌ. 5፡25፤ 2 ቆሮ. 12፡15፤ 11፡28-29።

## IV. የእግዚአብሔርን መንጋ በእረኝነት የሚንከባከቡ ሰዎች በእግዚአብሔር መሠረት በእረኝነት መንከባከብ አለባቸው—1 ጴጥ. 5፡2፦

ሀ. በእግዚአብሔር መሠረት በእረኝነት መንከባከብ እግዚአብሔር በባህርያቱ በሆነው ነገር መሠረት በእረኝነት መንከባከብ ነው—ሮሜ. 9፡15-16፤ 11፡22፣ 33፤ ኤፌ. 2፡7፤ 1 ቆሮ. 1፡9፤ 2 ቆሮ. 1፡12።

ለ. በእግዚአብሔር መሠረት በእረኝነት መንከባከብ በእግዚአብሔር ባሕርይ፣ መሻት፣ መንገድ እና ክብር መሠረት በሆነ እረኝነት መንከባከብ ነው እንጂ በእኛ ምርጫ፣ ፍላጎት፣ ዓላማ እና የግል ባሕርይ መሠረት አይደለም።

ሐ. በእግዚአብሔር መሠረት በእረኝነት ለመንከባከብ በሕይወት፣ በባሕርይ፣ በመገለጥ እና በአገልግሎት እግዚእብሔርን መሆን ያስፈልገናል—ዮሐ. 1፡12-13፤ 3፡15፤ 2 ጴጥ. 1፡14።

1. በእረኝነት በመንከባከባችን እኔነትን ከግል ባሕርይው እና ከልዩ ጠባዩ ጋር ሳይሆን እግዚአብሔርን እንድንገልጠው፣ የክርስቶስ ርቢ፣ የእግዚአብሔር መገለጥ መሆን ያስፈልገናል—ዮሐ. 1፡18፤ ዕብ. 1፡3፤ 2፡10፤ ሮሜ. 8፡29፤ ገላ. 4፡19።
2. እርሱ በሆነው መሠረት እና በኢኮኖሚው ባለው ግቡ መሠረት የእግዚአብሔርን መንጋ በእረኝነት በመንከባከብ አገልግሎቱ እግዚአብሔርን መሆን ያስፈልገናል—ኤፌ. 4፡16፤ ራእ. 21፡2።
3. ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ስንሆን በሕይወት እና በባሕርይ እግዚአብሔርን እንሆናለን ሌሎችንም በእረኝነት በመንከባከባችን እግዚአብሔር ነን—1 ዮሐ. 5፡11-12፤ 2 ጴጥ. 1፡4፤ 1 ጴጥ.5፡2።

## V. የክርስቶስን አካል የሚገነባው የእረኝነት እንክብካቤ የእርስ በርስ የእረኝነት እንክብካቤ ነው—1 ቆሮ. 12፡23-26፦

ሀ. በእረኝነት መንከባከብ ሁሉን-ያካተተ፣ በፍቅር የሆነ ለስላሳ እንክብካቤ ለመንጋው ማድረግ ነው—ዮሐ. 21፡15-17፤ ሐዋ. 20፡28።

ለ. አማኞች ሁሉ፣ መንፈሳዊ እድገታቸው ምንም ያህል ቢሆንም የእረኝነት እንክብካቤ ያስፈልጋቸዋል።

ሐ. እኛ ሁላችን በሕይወታዊዉ የክርስቶስ የእረኝነት እንክብካቤ ሥር መሆን እና ሌሎችን በእረኝነት ለመንከባከብ ከእርሱ ጋር አንድ መሆን ያስፈልገናል—1 ጴጥ. 2፡25፤ ዮሐ. 21፡16።

መ. በአብ ፍቅርና ይቅር ባይ ልብ መሠረት እና በወልድ በሚፈልግ፣ ፈልጎ በሚያገኝ እና በእረኝነት በሚንከባከብ መንፈስ መሠረት የእግዚአብሔርን መንጋ በእረኝነት መንከባከብ ያስፈልገናል—ሉቃ. 15፡4-24፣ 32።

ሠ. እርስ በእርስ በሆነ እረኝነት የሚንከባከቡና በእረኝነት የሚንከባከቧቸው በመሆን እኛ በጎችም እረኞችም ነን፤ በዚህ የእርስ በእርስ የእረኝነት እንክብካቤ በኩል አካሉ ራሱን በፍቅር ያንጻል—ኤፌ. 4፡16።

© 2020 Living Stream Ministry